እድሜያቸው11-18 ዓመት ለሆኑት ልጆችዎ ከአደገኛ በሽታዎች የመከላከያ መንገድ የ Tdap፣ MCVና HPV ክትባት መስጠት መሆኑን ሐኪሞች ያሳስባሉ።

- አንዳንድ ለሕጻናት የሚሰጡ ክትባቶች ለሙሉ ህይወት ዘመናቸው አይቆዩም። የ 11-18 ዓመት ልጅዎ ተጠብቆ እንዲቆይ ተጨማሪ ክትባቶች ያስፈልጉታል።

- አደግ ያሉ ሕጻናትና አዋቂዎች ባንዳንድ የተወሰኑ በሽታዎች የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ስለሆነ፣ አንዳንድ ክትባቶች ለነሱ ተብለው በልዩ ይሰራሉ። ዕድሜው 11-18 የሆነው ልጅዎ እነዚህን ክትባቶች ሕጻን እያለ አላገኛቸውም።

- ልጅዎ ጤነኛ ወይም ቀለል ያለ በሽታ ተይዞ ቢሆንም ክትባቶች ከአደጋ ነጻና መፍትሔ የሚሰጡ ናቸው።

የልጅዎን ሐኪም ስለነዚህ ክትባቶች ዛሬ ይጠይቁት!

ዕድሜያቸው 11-18 ዓመት ለሆኑ ክትባቱ በነጻ ነው

የአስተዳደር ክፍያ ሊጠየቁ ይችሉ ይሆናል፣ ቢሆንም መክፈል ካልቻሉ ምሕረት ይደረግልዎታል።

ክትባቱን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፤

- ሐኪምዎ፣ ነርስዎን ወይም ክሊንክዎን ያናግሩ
- Public Health – Seattle & King County ጋር በስልክ ቁጥር 206-296-4774 ይደውሉ

ልጅዎ በየዓመቱ የጤንነት ምርመራ እንዲያደርግ በጣም አስፈላጊ ነው!

ሐኪም፣ ነርስ ወይም ክሊኒክ ለማግኘት እርዳታ ለማግኘት የሚደውሉት ወይም የሚጎበኙት፤

Family Health Hotline
1.800.322.2588
711 (TTY relay)
Programs of WithinReach
www.ParentHelp123.org

Public Health
Seattle & King County

G2L GLOBAL TO LOCAL

በሌላ የተለያዩ መልኮችም ቀርበዋል
AMHARIC
2012

የ 11-18 ዕድሜ ልጅዎ ከአደገኛ በሽታዎች ተጠብቋልን?

የመኒንጅኮካል (ማጅራት ገትር) በሽታ

የመኒንጅኮካል በሽታ የአእምሮ ጉዳትንና ሞትን ሊያስከትል የሚችል አደገኛ በሽታ ነው።

- ከሕክምና እንክብካቤ ጋርም እንኳን፣ የህመም ምልክቶች ከታዩ በኋላ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሞትን ሊያስከትሉ ይችላሉ።
- በሽታው ከሰው-ወደ-ሰው በጉንፋን። መሳሳም ወይም እንደ የውሃ ጠርሙስ በመሳሰሉ አፍን ሊነኩ የሚችሉ ማናቸውንም ነገሮችን በመካፈል ሊሰራጭ ይችላል።
- በሽታውን ማንኛውም ሰው ሊያገኝ ይችላል፣ ቢሆንም በቡድን ስፖርት ሲጫወቱ ወይም በዶርሞች ውስጥ ሲኖሩ፣ ተጠጋግተው የሚኖሩ ወጣቶች በበሽታው የመያስ ከፍተኛ ዕድል አላቸው።
- የመኒንጅኮካል በሽታ በጠራራ ጸሓይ ወይም ሙቀት የሚነሳ ኣይደለም።

የ MCV ክትባት ከመኒንጅኮካል በሽታ ይከላከላል።

- ሐኪሞች ለልጆች 2 የ MCV ክትባት፣ ከ 11 ዕድሜ ጀምሮ እንዲሰጥ ያሳስባሉ።
- ለልጅዎ የ MCV ክትባትን ስለማስከተብ ሐኪምዎን ይጠይቁት!

ፐርቱሲስ (“ትክትክ”)

ፐርቱሲስ ለወራት የሚቆይ ሳል ሊያስከትልና መብላትን፣ መጠጣትን ወይም ማስተንፈስን ከባድ ሊያደርግ ይችላል።

- ፐርቱሲስ በቀላሉ ከሰው-ወደ-ሰው በሳልና በማስነጠስ ይሰራጫል።
- ከፍ ያሉ ሌሎች ልጆችና አዋቂዎች አብዛኛውን ግዜ ፐርቱሲስን ለሕጻናትና ነፍሰጡር ሴቶች ያሰራጨና ሞትን ሊያስከትል ይችላል።

የ Tdap ክትባት ከቲታነስ፣ ዲፕሴርያና ፐርቱሲስ ይከላከላል።

- ለሕጻናት የሚሰጠው የፐርቱሲስ ክትባት ለረጅም ግዜ ስለማይቆይ፣ የ Tdap ክትባት ዕድሜው 11 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ለማንኛውም ሰው እንዲሰጥ ሐኪሞች ያሳስባሉ።
- ለእርስዎና ለልጆችዎ የ Tdap ክትባትን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ሐኪምዎን ይጠይቁት!

ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV)

HPV የማሕጸን ነቀርሳንና የብልት ኪንታሮት መንስኤ ዋና ምክንያት ነው።

- HPV ያለባቸው ብዙዎቹ ሰዎች እንዳላቸው አያውቁም፣ ቢሆንም በግብረስጋዊ ግንኙነት ወደ ሌሎች ያሰራጨታል።
- HPV በጣም የተለመደ ነው። ቢያንስ ግማሾቹ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ በህይወት ዘመናቸው ውስጥ በበሽታው ይያዛሉ።

የ HPV ክትባት ከሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ በሽታንና ከማሕጸን ነቀርሳ ይከላከላል።

- የ HPV ክትባት ከማንኛውም የግብረስጋዊ ግንኙነት በፊት ከተሰጠ፣ አብዛኛውን የመከላከል ተግባሩን ይሰጣል።
- ለሴቶችና ወንዶች ሶስት ክትባቶች፣ ከ 11 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ እንዲሰጥ ሐኪሞች ያሳስባሉ።
- ለልጅዎ የ HPV ክትባትን ስለመስጠት ሐኪሙን ያናግሩት!